# በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

## የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች

**1/12/18**

- ከ ACPS የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያች ለምን አይደርሰኝም?
- አየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች ለወላጆች የሚደርሳቸው እንዴት ነው?
- ከ ACPS የሚላከውን የአውቶማቲክ የስልክና የቴክስት መልእክት ከሚቀበሉ ስም ዝርዝር ውስጥ በስህተት ወጥቻለሁ ። ተመልሶ መመዝገብ የሚቻለው እንዴት ነው?
- አንዳንድ ጊዜ ማስታወቂያዎች የሚዘገዩት ለምንድን ነው?
- በአካባቢያችን ያሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ዘግይተው ይከፍታሉ ወይም ይዘጋሉ ወይም በተቃራኒው ያደርጋሉ። እኛስ?
- መጥፎ አየር ንብረት አመሻሽ ላይ ዘግይቶ በሚመጣባቸው ቀናት ትምህርት ቤቶች ለምን አስቀድመው ይዘጋሉ?
- ትምህርት ቤቶች ለምን ተከፈቱ ?
- ከአየር ንብረት ጋር የተያይዙ ውሳኔዎች የሚሰጡበት የጊዜ ቅደም ተከትል ምንደን ነው?
- ትምህርት ቤቶች ዘግይተው የሚከፈቱ ከሆነ ትምህርት ቤት የሚጀመረው በስንት ሰአት ነው?
- ትምህርት ቤቶች ቀደም ብለው የሚዘጉ ከሆነ ትምህርት ቤት የሚቆመው በስንት ሰአት ነው?
- ከ ACPS አየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች ሲላኩ የካምፓኛና የመዝናኛ ማዕከላትን ሁኔታ ለምን አያካትትም?
- በሕንጻዎቻችን ላይ በርካታ ችግሮች የሚታዩት ለምንድን ነው? ACPS ስለ ጉዳዩ ምን እያደረገ ነው?
- የሚባክኑ የትምህርት ክፍለ ጊዚያትን ለማካካስ ACPS የሚያደርገው ነገር አለ?
- ወቅታዊ መረጃዎች ለማግኘት ምን ማድረግ እችላለሁ?

### ከ ACPS የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች ለምን አይደርሱኝም?

የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች የሚመለከቱ መረጃዎችን ለቤተሰብ ለመላክ የምንጠቀምበት ሲስተም የቤተሰብ አድራሻ የሚያገኘው ከ PowerSchool የመረጃ ማእከል ነው። በ PowerSchool የሚገኘው የእርስዎ መረጃ የተሞላ ካልሆነ ወይም ከተሳሳተ ማስታወቂያዎችን ሊያገኙ አይችሉም።

ወላጆችና አሳዳጊዎች የሚገኙበትን የስልክና የመኖሪያ አድራሻ ወቅታዊ መረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲኖራቸው የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። በእያንዳንዱ አዲስ የትምህርት ዓመት በ PowerSchool ያለውን መረጃ ያካተተ የእንኳን ደህና መጣችሁ ጥራዝ ለቤተሰቦች ይሰጣል። ወላጆችና አሳዳጊዎች እንደስፈላጊነቱን መረጃዎችን አስተካክለው ቅጹን ለትምህርት ቤቱ እንዲመልሱ ወይም በኮምፒውተር update their information online መረጃውን እንዲያስተካክሉ ይጠየቃሉ። ይህም መረጃ በትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር አማካኝነት ወደ መረጃ ማዕከሉ እንዲገባ ይደረጋል።




ከACPS መልእክት የማይደርስዎ ከሆነ PowerSchool (aka ACPS Academic Access - AAA) ውስጥ በመግባት የመገናኛ መረጃዎችን ትክክለኛነት ከታች በስተግራ በኩል ያለውን የተመላሽ ተማሪዎች ምዝገባ ሊንክ በመጠቀም የመገናኛ መረጃዎችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይቻላል። ወይም የትምህርት ቤትዎን ሬጅስትራር ዛሬውኑ ያነጋግሩ።

በ PowerSchool ያለው መረጃ ከተስተካከለ ከ24 ሰአት በኃላ ከACPS መልእክት መቀበል ይጀምራሉ።

### አየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች ለወላጆች የሚደርሳቸው እንዴት ነው?

አየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች በቅድሚያ በ ACPS website ድህረ ገጽ ላይ ይወጣል። አንድ ትምህርት ቤትን በተለይ የሚመለከት ከሆነ ማስጠንቀቂያው በትምህርት ቤቱ ድህረ ገጽ school's website ላይ ይወጣል። አንዳንዴ ደግሞ በሁለቱም ይወጣል።

እንደሁኔታው ቅደም ተከተልና እንደጉዳዩ ዓይነት፣ የኢሜልና ቴክስት መልእክት ልንልክ ወይም የአውቶማቲክ የስልክ ጥሪ ሊኖር ይችላል። ማስታወቂያዎች በሚከተሉት መንገዶችም ሊተላለፉ ይችላሉ፤

- ACPS ሶሻል መገናኛ ዘዴ በእንግሊዘኛ: Twitter | Facebook እና በስፓኒሽ : Twitter and Facebook ፣
- ACPS የአስቸኮይ መልእክት ስልክ: 703-866-5300፣
- ACPS-TV ፤ በአሌክሳንደሪያ ከተማ ቴሌቪዥን ኬቢል ቻናል 71 ፣
- በአሌክሳንደሪያ ከተማ ኢ ዜና (eNews): ዜናውን ለማግኘት በአሌክሳንደሪያ ከተማ ድህረ ገጽ አማካኝነት የእርስዎ ኢሜል አድራሻው መመዝገብ አለበት።
- የአካባቢው የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ጣቢያዎች።

የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች ከACPSበቀጥታ ሊያገኙ የሚችሉት PowerSchool up-to-date in PowerSchool ያለው መረጃ ወቅታዊ ሲሆን ነው።

## ከACPS የሚላከውን የአውቶማቲክ የስልክና የቴክስት መልእክት ከሚቀበሉ ስም ዝርዝር ውስጥ በስህተት ወጥቻለሁ ። ተመልሶ ለመመዝገብ የምችለው እንዴት ነው?

እባክዎን የአስቸኳይ መልእክት መመዝገቢያ ስልክ 855-502-7867 ይደውሉ።

### አንዳንድ ጊዜ ማስታወቂያዎች የሚዘገዩት ለምንድን ነው?

አስቸኳይ ወይም የድንገተኛ ሁኔታዎች ሲከሰቱ የእኛ የቅድሚያ ተግባር የተማሪዎቻችንን ደህንነት ማረጋገጥ ነው። ይህም ተማሪዎችን ካሉበት ወደ ሌላ አካባቢ ማጓጓዝ ፣ የድንግተኛ ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው እንደ እሳት አደጋ መከላከያ ሰራተኞች ጋር መመካከር ይጨምራል። የተማሪዎቻችንን ደህንነት ካረጋገጥን በኃላ መረጃ ማሰራጨት እንጀምራለን።

በመጥፎ አየርና መሰል ሁኔታዎች ትምህርት ቤቶች የሚዘጉ ከሆነ በእቅድ በተቀመጠው መሰረት የሚከናወኑ ስራዎች አሉ። የእነዚህ ዓይነት ጉዳዩችን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች ወዲያውኑ ሊሰራጩ ይችላሉ።

ከህንጻ ወይም ከፋሲሊቲ ጋር የተያያዙ በድንገት የሚፈጠሩ ሁኔታዎች የሥራ ሂደት ውስብስብና ብዙ ጊዜ የሚጠይቅ ነው። የሥራው ሂደት ብዙውን ጊዜ የሚከተሉትን ያካትታል፤:

- ስለጉዳዩ የመጀመሪያ መረጃ መቀበል፣
- ተጨማሪ መረጃዎች ማሳባሰብ፣
- ስለጉዳዩ መጠንና ስለሚያስከትለው ሁኔታ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ ከፋሲሊቲ፣ ከትራንስፓርት፣ አንዳንዴም እንደ አስፈላጊነቱ ከከተማው አስተዳደር፣ ከአጐራባች የአስተዳደር አካላትና ከባለሙያዎች ጋር ምክክር ይደረጋል።
- በቀጣይነት ምን መደረግ እንዳለበት ወይም ስለሚወሰድ እርምጃና ውሳኔ መስጠት፣ በጽ/ቤቱ ጊዜያዊ ኃላፊ (Interim Superintendent)
- የመረጃ ስርጭት እቅድ ማውጣት፣
- የወጣውን የመረጃ ስርጭት እቅድ በሥራ ማዋል ፣

መልእክቱን ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጐም በሂድቱ ላይ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል። ACPSአስቸኳይ ድንገተኛ መልእክቶችን በእንግሊዘኛ፣ እንዲሁም ከታቻለ በእስፓኒሽ፣ በአረብኛና በአማርኛ ያሰራጫል።

አንዳንድ ጊዜ እንደ ሁኔታው በቅድሚያ የተገኘውን መረጃ የምናሰራጭ ሲሆን ስለጉዳዩ ክትትል በማድረግ ተጨማሪ መረጃ እንደተገኘ በማስከተል እንዲሰራጭ ይደረጋል።በወላጅና በአሳዳጊዎች መውሰድ የሚኖርባቸው እርምጃዎች ካሉ ለምሳሌ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት መውሰድ ካስፈለገ አንቅስቃሴውን ለማቀናጀት ጊዜ ያስፈልጋል ፤ ምንጊዜም የተገኘው መረጃ የተሞላ መሆኑን ማረጋገጥና ወዲያውኑ እንዲሰራጭ ማድረግ የማመዛዘን ሥራ ይጠይቃል።

ተመሳሳይነት ሊኖር ቢችልም እያንዳንዱ ሁኔታ ልዩ በመሆኑ እንድጉዳዩ ዓይነት ተላዎዎጭ ተገቢ ምላሺ ይጠይቃል። ለምሳሌ ዝርዝር መረጃ ከመሰራጨቱ በፊት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት አስቀድመው እንዲውጡ ለማድረግ ወይም ትምህርት ቤት ለመዝጋት የተውሳሰበ የሎጀስቲክና የተለያዩ አካላትን የማስተባበር ሥራ ይጠይቃል። በዚህ ጊዜ መጀመሪያ በሚተላለፈው መልእክት የተሞላ መረጃ ለማግኘት አይቻልም። ሆኖም እንቅስቃሴው እየተለወጠ ሲሄድ ይህንኑ እየተከታተልን እናሳውቃለን።

**በአካባቢያችን ያሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ዘግይተው ይከፍታሉ ወይም ይዘጋሉ ወይም በተቃራኒው ያደርጋሉ። እኛስ?**




ትምህርት ቤቶችን ዘግይቶ የመክፈት ወይም የመዝጋት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አስቀድሞ በሌሊት አውቶብሶችን፣ የመኪና መንገዶችን፣ የእግር መንገዶችን፣ የአውቶብስ ማቆሚያዎችን፣ የትምህርት ቤት የመኪና ማቆሚያዎችን ሁኔታ የሚያጠኑት የትራንስፓርት ዳይሬክተር ፤ የትምህርት ቤት ህንጻዎችና ፋሲሊቲዎችን የሚመለከተውን የኦፐሬሽን ዳይሬክተር ፣ የአሌክሳንደሪያ የትራንስፓርት ሰራቶች በተጨማሪም አጐራባች የአስተዳደር አካላትን ጋር ስለ ሁኔታው ያላቸውን ግምገማ አስተያየት በመጠየቅ ምክክር ይደረጋል። በአጐራባች ካውንቲዎች የሚኖረው ሁኔታ በአሌክሳንደሪያ ካለው የተለየ ሊሆን ስለሚችል የእያንዳንዱ ጉዳይ የውሳኔ አሰጠጥ ራሱን ችሎ የሚከናወን ነው። አሌክሳንደሪያ ከአጐራባች ካውንቲዎች ስትነፃፀር በጣም አነስተኛ ናት። በትላልቅ የአስተዳደር አካላት የአየር ንብረቱ የሚለያይበት፣ የበረዶ ክምችት፣ የቅዝቃዜ መጠንና የተማሪዎች ረጅም ርቀት በእግር የሚጐዙበት ሁኔታ ስላለ ራቅ ባሉ አካባቢዎች በሚታዩ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ሊወሰን ይችላል።

የፌደራልና የአሌክሳንደሪያ መንግስት መ/ቤቶች መከፈት ወይም መዘጋት ለትምህርት ቤቶች መከፈትና መዘጋት ምክንያት አይሆንም።

**መጥፎ አየር ንብረት አመሻሻ ላይ ዘግይቶ በሚመጣባቸው ቀናት ትምህርት ቤቶች ለምን አስቀድመው ይዘጋሉ?**

**አውቶብሶች ፤** የመዋእለ ህጻናትንና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን የሚያገለግሉት አውቶብሶች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችንም ያገለግላሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን የማመላለሱን ሥራ እንደጨረሱ አውቶብሶች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይቀጥላሉ። በመደበኛ የትምህርት ቀን ከሰዓት በኃላ የመጀመሪያ የአውቶብስ እንቅስቃሴ በ2:35 ፒ.ኤም የትምህርት ቤቱን ግቢ ይለቃል። በመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመደበኛው ትምህርት ውጭ የሚካሄዱ ተግባራት የመጨረሻው የማጓጓዝ ሥራ ከምሽቱ 7:00 ፒ.ኤም በኃላ ይጠናቀቃል።

ትምህርት ቤቶችን አስቀድሞ በመዝጋት፣ ከመደበኛው ትምህርት ውጭ የሚካሄዱ ተግባራት በመሰረዝና በአውቶብሶች የማመላለሱን ሥራ አስቀድሞ በማጠናቀቅ ፀሐይ ጠልቆና ቅዝቃዜው ጨምሮ ሁኔታዎች አስከፊ ከመሆናቸው በፊት ተማሪዎቹን በሰላም ወደ የቤታቸው መድረሳቸውን ለማረጋጋጥ የታቀደ ነው። የአየር ንብረት ትንበያው እውን የማይሆንባቸው ቀናት አሉ። ሆኖም

ለተማሪዎቻችን ደህንነት ቅድሚያ የምንሰጥ ሲሆን ውሳኔ ላይ የምንደርሰው ውሳኔ መስጠት በሚያስፈልግበት ጊዜ በወቅቱ በምናገኘው መረጃ ተመስረተን ነው።

## ትምህርት ቤቶች ለምን ይከፈታሉ?

አንዳንድ ጊዜ ትምህርት ቤቶችን ለመክፈት የምናደርገው ውሳኔ ጥያቄ እንደሚያስነሳ እናውቃለን። ለምንድን ነው ትምህርት ቤቶችን በሰዓቱ ለመክፈት የምንወስነው ?

ተማሪዎቻችን ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱት ለመማር ሲሆን የእኛ አላማም የትምህርት ክፍለ ጊዜን በመጨመር እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ እዲሆን ማድረግ ነው። በተጨማሪ ACPSከ63% በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች በነፃ ወይም በዝቅተኛ ክፍያ ምግብ የሚያገኙ ናቸው። በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ቁጥሩ ከዚያም በላይ ነው። አብዛኛዎቹ ተማሪዎችና ቤተሰብ ከትምህርት ቤት የሚያገኙት ምግብ ውሳኝነት አለው። በእያንዳንዱ ቀናት የትምህርት ቤት መክፈቻ ሰዓት መዘግየት፣ አስቀድሞ ወይም ጠቅላላውን መዘጋት ምክንያት እነዚህ ተማሪዎች የእለቱን ምግብ አያገኙም። ዝጉ አርብ ቀን ከሆነ በሳምንቱ መጨረሻ ወደ ቤት የሚወስዱትን ምግብ ያጣሉ።

በተቻለ መጠን ትምህርት ቤቶቻችንን ክፍት ማድረግ የትምህርት ክፍለ ጊዜን ከመጨመር በተጨማሪ የእነዚህን ተማሪዎች ጤንነትና ደህንነት ለማረጋጋጥ ይረዳል።

## ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች የሚሰጡብት የጊዜ ቅደም ተከትል ምንደን ነው?

ከአየር ንብረት ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤቶች ለመዘጋት ሁኔታው እንደፈቅደ ከጥዋቱ በ5:30 ኤ. ኤም መረጃውን ለማሰራጨት እንሞክራለን። ትምህርት ቤቶች አስቀደሞ መዝጋት ሲያስፈልግ ከጥዋቱ 11:00 ኤ. ኤም ማስታወቂያ ለማውጣት እንሞክራለን። ሆኖም ይህን ሰዓት ሁሌም ለመጠበቅ አይቻልም። አንዳንድ ጊዜ ትምህርት ሊጀመር ጥቂት ደቂቃ እስከሚቀረው ድረስ ስለሁኔታዎች ምንም ላናውቅ እንችላላን። ACPS ያገኘውን መረጃ በተቻለው ፍጥነት ለእርስዎ ያስተላልፋል።

## ትምህርት ቤቶች ዘግይተው የሚከፈቱ ከሆነ ትምህርት የሚጀመረው በስንት ሰዓት ነው?

የመዋእለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል እና የቨርጂኒያ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ኢኒሼቲቭ (VPI) ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት ሁለት ሰዓት ዘግይተው ይጀምራሉ።

ቅድመ መዋእለ ህጻናት የጦት ፕሮግራም (የልጆች ልዩ ቅድመ ትምህርትና ቅድመ መደበኛ ትምህርት) የጥዎት ተማሪዎች ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት ሁለት ሰዓት ዘግይተው ይጀምራሉ። እንዲሁም አንድ ሰዓት ዘግይተው ይወጣሉ።

የቅድመ መዋእለ ህጻናት የከሰዓት በኃላ ተማሪዎች ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት አንድ ሰዓት ዘግይተው በመጀመር ለሁለት ሰዓታት ይቆያሉ።

## ትምህርት ቤቶች አስቀድመው የሚዘጉ ከሆነ ትምህርቱ የሚቆመው በስንት ሰዓት ነው?

አስቀድሞ ሲዘጋ ተማሪዎች የሚለቀቁበት ጊዜ ከመደበኛው የትምህርት ማብቂያ ሁለት ሰዓት በፊት ነው። የጥዎት ቅድመ መዋእለ ህጻናት ትምህርት ጥዎት በ 11:00 ኤ.ኤም ይጠናቀቃል። የከሰዓት በኃላ ቅድመ መዋእለ ህጻናት ትምህርት ይሰረዛል። ሆኖም የማካካሻ ሌላ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሊዘጋጅ ይችላል።
ትምህርት ቤቶች ለሙሉ ቀን ሲዘጉ ከትምህርት በኃላ የሚኪያሄዱ ተግባራትና የስፓርት እንቅስቃሴዎች በሙሉ ይሰረዛሉ።

## ከACPS አየር ንብረት ማስጠንቀቂያና የድንገተኛ ሁኔታዎች ማስታወቂያዎች ሲላኩ የካምፓኛና የመዝናኛ ማዕከላትን ሁኔታ ለምን አትጨምሩም?

በርካታ ቤተሰቦች ከትምህርት ጊዜ ውጭ የካምፓኛና የመዝናኛ ማዕከላት አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሆኑ እናውቃለን። እነዚህ ፕሮግራሞች ሲቆረጡ ብዙ ነገር ይስተጓጉላል። የካምፓኛና የመዝናኛ ማእካላት ሁኔታን የሚመለከቱ የመረጃ ስርጭት እስከ አሁን መሆን እንደሚገባው አይደለም። ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል አሰራራችን በመቀየር ላይ ነን።

ውሳኔ በምንሰጥባችው ወቅቶች የካምፓኛና የመዝናኛ ማእካላት ሁኔታ የሚመለከቱ የመረጃ የማይገኙበት አጋጣሚ አለ። የመዝናኛ ማዕካላትና የካምፓኛና ACPS ስር አይተዳደሩም። የራሳቸውን ውሳኔ ይሰጣሉ። የትምህርት ቤቶች አስቀድሞ ስለመዘጋት በአስቸኮይ ለማስተላለፍ ስንጥር በመጀመሪያ በሚሰራጩ መልእክቶች አልፎ አልፎ ይህን መረጃ ለማካተት አንችልም። ሆኖም እንዲረዱልን የምንፈልግው  በእንደዚህ ዓይነት ወቅቶች ከሁለቱም ድርጅቶች ጋር ሁልጊዜም የምንገናኝ ሲሆን በተቻለ ፍጥነት መልእክቱን ለማሰራጨት እንሰራለን።

የካምፓኛና ሁኔታ የሚመለከቱ መርጃ ድርጅቱ በቀጥታ ለቤተሰቦች በቀጥታ የማስተላለፍ ሃላፊነት አለበት። ስለ ሁኔታው እርግጠኛ ካልሆኑ በ 703-549-0111 ስልክ በቀጥታ ይገናኙ።በተጨማሪም @CampagnaCenter on Twitter መከታተል ይችላሉ።

ACPS ትምህርት ቤቶች ስለሚኪያሄዱ የመዝናኛ ማእካላት ፕሮግራሞች ሁኔታ የአሌክሳንደሪያ ከተማ ፓርክና የመዝናኛ ማእከል ፌስ ቡክ ገጽ ተመልከቱ ወይም 703-746-4343 ይደውሉ።.

ስለሁለቱም ፕሮግራሞች ሁኔታ መረጃ እንደተገኘ በመልከታችን ውስጥ እናካትታለን።

## በሕንጻዎች ላይ በርካታ ችግሮች የሚታዩት ለምንድን ነው?

ትምህርት ቤቶቻችን በጣም ያረጁ ናቸው። ከ1966 ወዲህ የተገነቡት ሶስት ትምህርት ቤቶች ናቸው።አንደኛውም ገና በመሰራት ላይ ይግኛል። ያሉን ያረጁ ፋሲሊቲዎች ሲሆኑ ለዓመታት እነዚህን ዘመናዊ ለማድረግ በቂ በጀት አላገኘንም።

አብዛኛውን የምሥራቁን ጠረፍ በሸፈነው ቀዝቃዛ አየር ምክንያት በተለይ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ችግሩ ተባብሶል። በተከታታይ ከዜሮ በታች የነበረው ቅዝቅዜ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታውቅ ሁኔታ እድሜ የጠገቡ ፋሲሊቲዎችን ተፈታትኖል።   ያረጁ የHVAC መሳሪያዎች በሚቀዘቅዝበት ሰዓት ስራቸውን ለማከናወን ተቸግራዎል።.

የትምህርት ቤቶች ፋሲሊቲዎች ቡድን HVAC መሳሪያዎችን ከሚጠገኑ ከኮንትራክተሮች ጋር ያለማቋረጥ እየሰሩ ነው። ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በየትምህርት ቤቶቹ ሙቀት መኖሩን ለመመልከት ቀደመው ይገኛሉ። ትምህርት ቤት በተዘጋበትና በሳምንት መጨረሻ የእርፍት ቀናት የፋሲሊቲ ሰራተኞች በየትምርት ቤቱ በመገኘት ሲመለከቱ ነበር።

ይህ ሁኔታ በተማሪዎች የትምህርት ሂደት ላይ ስላለው ተጽእኖ ያለዎትን ቁጭት የምንገነዘብ ሲሆን ተማሪዎቹ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀናት ምቹ የሆነ ክፍል እንዲያገኙ የጋራ ግባችን መሆኑን እንዲያውቁልን እንወዳለን።

## ACPS  ስለ ጉዳዩ ምን እያደረገ ነው?

በበጋው ወቅት ሰፊ የጥገና ፕሮግራም በትምህርት ቤቶች በተለይም ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ በሚመጣበት ወቅት ችግር በሚያጋጥማቸው  እንደ ጆርጅ ዎሽንግተን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ያሉትን ቅድሚያ በመስጠት ይከናወናል።

ጃንዎሪ 17 አዲሱን የACPS ዋና የስራ አስፈጻሚ Mignon Anthony አቀባባል ያደርጋል። Mignon Anthony  የትምህርት ፋሲሊቲዎችን የረዥም ጊዜ እቅድ በማዘጋጀት ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ሲሆን የተለያዩ የስራ አፈጻጸም አካላት፤ የትራንስፓርት፣ የህንጻ አጣቃቀምና አያያዝ ጨምሮ የፕሮግራሞችን ሂደት ብቃትና ጥራት የማረጋገጥ ስራ ያከናውናሉ። ቅድሚያ የሚሰጡት ዋና ሥራ ያረጁ ፋሲሊቲዎችን ጥገና መከታተል ይሆናል።

## የሚባክኑ የትምህርት ክፍለ ጊዚያት ለማካካስ ACPS የሚያደርገው ነገር አለ?

ከመደበኛ ሰአቱ አስቀደሞ ለሚዘጉ ተጫማሪ የማካካሻ የትምህርት ጊዜ አይኖርም። የቨርጅኒያ የትምህርት ዲፓርትሜንት በአንድ የትምህርት ዓመት 180 የትምህርት ቀናት ወይም 990 ሰዓታት መኖር እንዳለብት ይደነግጋል።

የመጀመሪያ 3 የበራዶ ጊዜ ዝግ ወይም ትምህርት ቤት ለሚዘጋባዝቸው ቀናት ተጫማሪ የማካካሻ የትምህርት ጊዜ አያስፈልግም።ስድስተኛና ሰባተኛ ቀናት እንደዚሁ አያስፈልግም። ከዚህ ውጭ ላሉ ትምህርት የሚቆረጥባቸው ቀናት የማካካሻ የትምህርት ጊዜ መዘጋጀት ይኖርባታል።
የበራዶ ጊዜ ዝግ ተጫማሪ የማካካሻ የትምህርት ጊዜ በ [ACPS calendar](ACPS calendar) የጊዜ ሰሌዳ ተካቶል።

ከዘጠኝና ከዚያ በላይ ቀናት ትምህርት ከተቆረጠ ተጫማሪ የማካካሻ የትምህርት ጊዜ ስለማስፈለጉ ወይም በስቴቱ ደንብ መሰረት የትምህርት ጊዜውን በበቂ ያሞላ ስለመሆኑ አጠቃላይ የማስተማሪያ ጊዚያት ግምገማ ይደረጋል።
ጆን አዳምስ የመጀመሪያ ትምህርት ቤት፣ በፍራንሲስ ሲ ሐመንድና በጆርጅ ዎሽንግተን መካከላኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአላፉት ሁለት ሳምንታት ስለተቆረጠው ጊዚያት ሊኖር ስለሚችል አማራጭ ከየትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ሰራተኞች ጋር በመነጋገር ተጫማሪ የማካካሻ የትምህርት ጊዜ ካስፈላገ ለቤተሰብ እናሳውቃለን።

## ወቅታዊ መረጃዎች ለማግኘት ምን ማድረግ እችላለሁ?

- PowerSchool የሚገኘው መረጃ ወቅታዊ መሆኑን ይመልከቱ፣ ካልሆነ ወቀታዊ አድርጉ ወይም ለትምህርት ቤቱ ሬጂስትራር ስልክ ይደውሉ። Check your information in PowerSchool

- የድህረ ገጻችንን በመጐብኘት የድንገተኛ ሁኔታዎች ወቅት ስለሚከናወኑ ስራዎች emergency procedures በመመልከት በዚህ ወቅት ምን ማድረግ እንደሚኖርብዎ ተረዱ።

- የድንገተኛ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ወቅት የልጆቹን ደህንነት ለመጠበቅ ከእኛ ጋር አብረው ያለችግር እንዲሰሩ ለልጅዎ ስልክ ከመደወል ወይም ቴክስት ከማድረግ ይቆጠቡ። ይህም የተዘባራረቀ መርጃ ስርጭትና ግራ መጋባት እንዳይፈጠር ያግዛል። የ ACPS የድንገተኛ ሁኔታዎች የመገናኛ መንገዶች ACPS emergency communications channels የድንገተኛ ሁኔታዎች ወቅት ዋነኛው የመገናኛ መንገድ ነው።

- የድንገተኛ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ወቅት ልጅዎን ከአደጋ በመጠበቅ ላይ ማተኮር እንድንችል እባከዎን ለትምህርት ቤቱ ስልክ አይደውሉ ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ አይሂዱ።

- የድንገተኛው ሁኔታ ካለፈ በኃላ ተጨማሪ ትክክለኛ መርጃ ማግኘት ከፈለጉ እባክዎ ትምህርት ቤቱ call your school ወይም የኮሚዩኒኬሽን ቢሮ 703-619-8003 በቀጥታ ይደውሉ። እንዲሁም የድንገተኛ ሁኔታዎች ዋነኛ የመገናኛ መንገዶች official ACPS channels of communication ይጠቀሙ።

- የ PTA አባል ይሁኑ እንዲሁም ACPS ይደግፉ።